# ሁለቱ ዶክተሮች

እኛው ተለያይተን
እኛውን አዳክመን
እኛው ተጠላልፈን
እኛን አነቅፈን
ሽንፈትን ሰንቀን
እኛው በእኛው ወድቀን
እኛው ተነጣጥለን
ክፍተት አበጅተን
ልዩነት አጉልተን
መማማር ተስኖን
ከራሳችን ስህተት
ተመክሮ አግኝቶ
ጠፍቶን መላ መምታት
ባህሪያችን ሆኖ
ልዩነት አፍቅሬ
እያደሩ ጥጃ
እየፈጩ ጥሬ!!!
በስህተት ላይ ስህተት
ዳግም ልንሰራ
ተነጣጥለን ቆመን
ሆነን ተነፋራ
አንድም ተጮበርብረን
አንድም ስንፈራ
የሞተ አምባገነን
ህይዎት እንዲዘራ
ራሳችን ሚቾች
ራሳችን ገዳይ
አርገነው ነገሩን
ዐይን እራሱን አያይ
ስንወነጃጀል ጀንበር በሰረቀ
ድምጻአችን ተቀማ ድሉም ተነጠቀ::

የሰከነ ዕይታ ከድቶን ቅንነት
አንድም በሆድ አደር ወይ እበላ ማለት
አለያም ለሀገር ከራሳችን በላይ
ድንቁርና ጋርዶን አርቀን እንዳናይ
አሽኬላ እየሰራን እኛው ለኛው ወጥመድ
ትግላችን ውጤቱ ግቡ እንዲሸመደመድ
የራሳችን ጠላት እራሳችን ሆነን
እኛው እኛን ገድለን
በወገናችን ላይ በሬሳው ተራምደን
ህዝብንና አገርን አዋርደን ተዋርደን
ለሽራፊ ስልጣን ለጥቅም ተገዝተን
አንድም ከቂም በቀል ከቁርሾ ተነስተን
ወይም ከራዒ እጦት ወይ ከክህሎት መጉደል
ባጋጣሚም ይሁን ወይ ባለመታደል
የገጠመን ዕድል ለሶስተኛ ጊዜ
ባለብን በሽታ የማግለል አባዜ
ለድጋሜ ለንደን_ለድጋሜ ግንቦት
በሚዳርግ ሴራ ህዝቡን ለባርነት
ግጥም አርገው አስረው ህዝቡን እግር
ከወርች
ለአሜሪካ ሸጡን ሁለቱ ዶክተሮች!!!
ሰኔ 1998

abraham beyenne